# ያባይ ነገር

ኃይሌ በላይ
(ኦታዋ - መስከረም 1997 ዓ.ም.ኢ)

እረ ያባይ ነገር
ለማን አቤት እንበል
ለማንስ እንንገር
ተራራ ፈንግሎ
ዛፎችን ገንድሶ
አፈሩን፣ ማዕድኑን
መሬቱንም አርሶ
ያለ ምንም ፈቃድ
ያገር ወሰን ጥሶ
ያለ የሌለዉን
በሙሉ አግበስብሶ
ሰዉ ቤት ገብቶ ያድራል
ቀን ተሌት ገስግሶ፤

ድንገት እግር ጥሎኝ
ግብጾች ሃገር ብሄድ
ሰዎች ይግረማችሁ
አየሁላችሁ ጉድ
የተወለደባት
የመነጨባትን ሃገር
በፍፁም ሳይፈራ
እንዳይሆንበት ጡር
ሃብትዋን አግበስብሶ
እየዛቀ አፈር
እያጉረመረመ
ፈጥኖ እሚወረወር
ለካስ ለማበልፀግ
ኖርዋል የሰዉ ሃገር፤

ጉድ ነዉ
እረ ጉድ ነዉ!
ሌላ ምን ይባላል
ወላጅ እናት ጥሎ
ጎረቤትን ማክበር
ትዝብትም ሳይፈራ
እርግማንም ከቶ
ተንጣሎ ተኝትዋል
ተሰዉ ሃገር ገብቶ፤

አባይ!
እዉነት ያንተ ነገር
ለወሬ አይመች
ለሰዉ አይነገር
እረ መልስ ስጠኝ
እስቲ ልጠይቅህ
ባይመችህ ነወይ
ኑሮ ቢቸግርህ
ያላንዳች ይሉኝታ
ምንም ቅር ሳይልህ

በወላጅ እናትህ
እንዲህ መጨከንህ!
ወይስ ተቀይመህ
ስላልሰራንብህ
እጃችን አጣምረን
ዝም ብለን ስናይህ
ጉዳትህን እረስተን
በከበሮ እምቢልታ
ኣባዬ! ኣባዬ!
እያልን በዕልልታ
ስንሸኝህ በእስክስታ፤

ቢሆንም!
ስማኝ ያገሬ ወንዝ
ቁም ነገር ልንገርህ
ቤትህን ጥለህ መሄድ
ለመቼም አይበጅህ
አልሰማህ እንደሆን
ያባቶች ተረት
የሰዉ ቤት የሰዉ ነዉ
ከቶ አይሆንም ንብረት፣

እነሱም ቢሆኑ
የሚያመሰግኑህ
በቀን አሥር ጊዜ
የሚሰግዱልህ
አባይ ንጉስ ብለዉ
የሚያሽቃብጡህ
ጥቅማቸዉን አዉቀዉ ነዉ
ሌላ እንዳይመስልህ፤

ባባይ ተናገርኩ እንጂ
ከቶ እኛስ ብንሆን
መች አርፈን ተቀመጥን
ሃገራችን ብለን
በስደትም ይሁን
ትምህርት ፍለጋ
ሃገር ጥለን ወጥተን
በክረምት በበጋ
በአራቱ ማዕዘናት
የዐለማችን
እንኖር የለም ወይ
ተበታትነን፤

እናት ሃገራችን
ደጉዋ ኢትዮጵያ
አሳድጋ አስተምራ
በጥበብ በሙያ
ደረሱልኝ

ልጆቼ እያለች
ስትጠብቅ በተስፋ
የተማረዉ ሁሉ
ሃገር ጥሎ ጠፋ፤

ደሃይቱ ሃገር
ፈላጊ ዕርዳታ
ምሁር አልባ ሆና
ሁሌ ስትንገላታ
ልጆችዋ በሙሉ
ጎበዝ የሆኑት
በዕውቀት በትምህርት
ልቀዉ የመጠቁት
ሃገር ጥለዉ ወጥተዉ
በሚያፈሩበት
አገልጋይ ሆነዋል
ላብታም ሃገራት፤

የኣባይን መሸሽ
ሲገርመኝ እየኖረ
በጣም የሚጎዳ
ከሬት የመረረ
የመጥፋቱ ጉድ ነዉ
ባገር የተማረ፤

እህቶች ወንድሞቼ
አድምጡ ነገሬን
ይህን ያባይን ጉድ
እስቲ እንየዉ አብረን
እሱ እንደሆን አይሰማ
ምንም ጆሮ የለዉ
መፍሰሱ አይቀርም
ዝም ብለን ካየነዉ
ምንም ብንዘፍንለት
ብናባብለዉም
መማፀን መፀለይ
ትርጉም አይሰጠዉም
ስለዚህ እናስብ
መዝፈኑን ቀንሰን
መፍትሔ እናቅርብ፤

በሌላዉም በኩል
በስደት ያለነዉ
በትምህርት በዕዉቀት
ልቀን የመጠቅነዉ
በቅርቡም ብንሆን
ወይም ከርቀት
እናት ኢትዮጵያን
ከልብ እናስባት፣

ኣንገትዋን እደፍታ
ወደ ታች እያየች
ዐይኖችዋን ሸፍና
በንባ እየታጠበች
እናት ታለቅሳለች
ልጆቼ! እያለች
በደከመ አንደበት
እኛን ትጣራለች
በተስፋ በእምነት
ትጠብቀናለች
ምን እንመልስላት፣

የመሠረትነዉን
የተመቸ ኑሮ
ጥለንም ባንሄድ
ወዳገር ቤት ጉዋሮ
ባገኘነዉ ትምህርት
በገበየነዉ ዕዉቀት
መንገድ እንፈልግ
አቤት የምንልበት
ኑሮአችንን ትተን
መሄድ ባንችልም
እጃችንን እንዘርጋ
በተቻለ ዐቅማችን
ለዚሁም መመሪያ
መንገድ እንዲሆነን
ውድ ሃገራችን
እንዳትባል መካን
ቢዮንድ ሴማንቲክስን
እናንብብ ጠንቅቀን፤

ኣባይም ሄዶባት
እኛም ጠፍተንባት
ወልዳ እንዳልወለደች
ችግር ያማቐቓት
ሆና እንዳትቀር
እናት ሃገራችን
አለንልሽ እንበላት
ካለንበት ሆነን
እስዋም ደስ እንዲላት
እኛም ባለንበት
እንዲሰማን ኩራት፤

ስሙኝ ወንድሞቼ
እህቶቼም በህብረት
ቅድም የጠቀስኩት
ያባቶችን ተረት
ላባይ ብቻ አይደለም
እኛም አለንበት፡፡